በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ
አዲስ አበባ - ኢትዮጲያ

**Federal Democratic Republic of Ethiopia**
**Ethiopian Civil Service University**
**Addis Ababa – Ethiopia**

ቁጥር፡- ቅበላ 001/03/838/11
ቀን፡- ነሐሴ 29 /2011 ዓ.ም

- ለአመራር አስተዳደር ኮሌጅ
- ለፋይናንስና ሥራ አመራር ልማት ኮሌጅ
- ለከተማ ልማት እና ምህንድስና ኮሌጅ

ጉዳዩ፡- __በ2012 የትምህርት ዘመን በሁለተኛ ዲግሪ በቅዳሜና እሁድ እና በማታ መርሀ ግብር ወደ ዩኒቨርስቲ የሚገቡ ዕጩዎችን ይመለከታል፡፡__

ዩኒቨርስቲያችን ለ2012 ዓ.ም በሁለተኛ ዲግሪ ትምህርት በቅዳሜና እሁድ እና በማታ መርሀ ግብር በተለያዩ ዲፓርትመንቶች ተቀብሎ ለሚያስተምራቸው ዕጩዎች ሰኔ 1 እና 2 ቀን 2011 ዓ.ም የመግቢያ ፈተና መስጠቱ ይታወሳል፡፡ በዚሁ መሠረት ከተወዳዳሪዎቹ መካከል በመግቢያ ፈተና ዉጤታቸው መሠረት ወደ ዩኒቨርስቲዉ እንዲገቡ የተመረጡትን ዕጩዎች የስም ዝርዝር ___ገጽ በዚህ ደብዳቤ ሸኚነት መላካችንን እንገልጻለን፡፡

**የምዝገባ ቀን :**

- **ለማታ ተመዝጋቢዎች መስከረም 29 እና 30 ቀን 2012 ዓ.ም.**
- **ለቅዳሜና እሁድ ተመዝጋቢዎች ጥቅምት 1 እና 2 ቀን 2012 ዓ.ም.**
- **ዘግይተው የሚመጡ በቅጣት ጥቅምት 3 ቀን 2012 ዓ.ም. ብቻ ይሆናል፤**

**የምዝገባ ቦታ** : ሲኤምሲ መንገድ በሚገኘው በዩኒቨርስቲው ዋና ግቢ፤

**የዕጩዎች ለምዝገባ በሚቀርቡበት ጊዜ፡-**

- ሁለት ጉርድ ፎቶግራፍ፣
- የመመዝገቢያ እና የሴሚስቴር የትምህርት ክፍያ፤
- የመጀመሪያ ድግሪና የውጤት ማስረጃ (Student Copy) ዋናዎቹና አንድ አንድ ፎቶ ኮፒ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡
- እንዲሁም የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን ካገኙበት የከፍተኛ ትምህርት ተቋም Official Transcript በዩኒቨርስቲያችን የፖስታ ሣጥን ቁጥር 5648 ከምዝገባው ቀን አስቀድሞ እንዲላክ ማድረግ አለባቸው፡፡
- ዕጩዎች የሚመዘገቡት በግንባር ሲቀርቡ ብቻ ነው፡፡
- ከምዝገባው ቀን አስቀድሞም ሆነ ዘግይቶ የሚመጡና የዲፓርትመንት ለውጥ ጥያቄ የሚያቀርቡ ዕጩዎችን አናስተናግድም፡፡

__ማሳሰቢያ፡-__

1. ኦፊሻል ትራንስክሪፕት አስቀድሞ ወደ ዩኒቨርስቲው ያላስላከ ማንኛውም አዲስ ተማሪ መመዝገብ የማይችል መሆኑን በጥብቅ እናሳስባለን፡፡
2. በተማሪዎች ቁጥር ማነስ ምክኒያት የተወሰኑ ዲፓርትመንቶች ከማታው መርሃ ግብር ወደ ቅዳሜና እሁድ መርሃ ግብር ተቀላቅለው እንዲማሩ የተወሰነ መሆኑን አስቀድመን እንገልጻለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

Alemayehu Seberu
Director, Students Admission Office

__ግልባጭ፡-__

- ለፕሬዝዳንት ጽ/ቤት
- ለአካዳሚክ ጉዳዮች ምክትል ፕሬዝዳንት ጽ/ቤት
- ለተከታታይና ርቀት ትምህርት ማስተባበሪያ ዳይሬክቶሬት
- ለሬጅስትራር ጽ/ቤት
- ለቤተመጽሐፍትና መረጃ ማእከል

__ኢ.ሲ.ሰ.ዩ__

☎ ስልክ (Tel) 0116 46 30 15 President 0116 463012 Academic Vice President 0116 463013 ቴሌ ፋክስ (Fax) 0116 463016
D & A Vice President 0116 462348 External Relations Office 0116 462344 ✉ P.O.Box ፖ.ሣ.ቁ. 5648
Website: www.ecsc.edu.et E-mail: ecscpro@ecsc.edu.et